“አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ።”

ለአቶ አምሳሉ ግ/ኪዳን “መልሳቹህ” ለምሉና ሌሎችም በተመለከተ የቀረባ፡

ከቃሉ ኩማ 10/04/2014

ወንድሜ ህይ! በመጀመሪያ አነሳስህ ታሪክ መሰረተድርገህ ነው የተንቀሰቀስከው። አሁን ግን ሰበካውን፡ ፖላቲካውን፡ ታሪኩን(ተረት-ተረት)፡ የትምክህትና የንቀት ቀለቶችህ ተበውዘው ሊክ እንደካርታ ጨዋታ አኬር (ጆከር) ፍለጋ የሚባዝን ሰው መሰልከኝ። አሁን በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንድ ያኔው 19ኛ ክፍለ ዘመን ብዙ የተናገራ እንድሚያሸንፍ አይደለም። አማሪኛችሁን ስለ ከሽንክና በጥሩ ቃላቶች ነገሮችን ስለ ሸፋፈንክ (ቅኔም) እንበለው፡ ሃቁ ተደብቆ አይቀርም።

ከመጀመሪያም ጽሁፎችህ ያጠናጠኑት በአኖሌ ታሪክ፡ በምንሊክና በአድዋ ጦርነት ስለ “ሐበሻ-ኢትዮጵያ” በተመለከተ ነበር።  በሳለፍናቸው ሳምንታት እኔ ደግሞ በስንት ወጭና እንድሜየን ጨርሼ በገዛሁት አማሪኛዬ ሰባብሬም ብሆን ያለውን ሃቅ ለማቀረብ ሞክራለሁ። ሌሎችም በተቻላቸው መጠን ሊመልሱልህ ሞክረዋል። ያ ሁሉ አልተዋጠልህም። ሊታምናን አልቻልክም። ይህም ሁለት ሰበብ አለው አንድ ፊደላችሁን በትክክል ለማስቀመጥ በጣም ይከብዳል። አማሪኛውም ከብዙ ቁዋንቁዋዎች ስለተቀየጣ (ከኣረቡ ከይብራይስጡ፡ ከግዕዙና የኩሽ ህዝቦችኝ) በጣም ይከብዳል። ለዚህም ነው ከ1270ዎቹ ጀምሮ እስካሁን ተሰርቶበትም ምንም እንድገት ያላሳየው። በመሆኑም ነው ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ከኃላ ተነስተው በሁሉም ነገር የቀደሙንና ያደጉትም። ለዚህም ነው አንተው እንዳልከው ለመረዳዳት ያልቻልነው። ለማንኛውም አሁንም ብታምነኝም ባታምነኝም በዚቹ በደካማ አማሪኛዬ ለማስረዳት እሞክራለሁ። ነገር ግን አንተ ላታምነኝ ትችላለህ። ምክንያቱም ሊክ እንደተረታችሁ “ሌባ እናት ልጅዋን አታምንም” የሚባለውን ብህላችሁን ያሳየናል። ምክንያቱም ከዚህ በፊት መላልሼ እንደጸፍኩልህ ደብተራዎቻችሁ የደራረቱት ልቦዋለድ ታሪኮች አዙሪት ውስጥ ስለገባችሁ፡ ከዚያ አዙሪትም መውጣት ጭንቅ ሆናባችሁ። እኔ ግን ታሪኮችን መሠረት አድርጌ ነው ጽሁፎቼን ሳቀርብልህ የነበረው። አንተ ግን አንዴ “ፈረንጁን አትመነው” ትላለህ። አንዴ ደግሞ “የአገራችን ጸሃፊዎች ካላመንክ የውጪው ዓለም ጸሃፊዎች አትመው ያለፉትን አንብብ” ትለኛለህ። እኔ ግን እንካሁን ድረስ እየጸፍኩልህ ያለሁት ከሁለቱም ወገን የተሻለውን በመጠቀም ነው ሐሳቤን ለማስተላለፍ የምከርኩት።

እኔ እንዳነበብኩት አብዛኛው የውጪ ጸሃፊዎችም ለአቢሲኒያውያን ያዳለ መልዕክት ያለውን ነው የጸፉት። ወይም በወቅቱ በሥልጣን ላይ የነበረው ንጉሳችሁ ወይም የእሱ አዋዳሾች የነገሩትን እየጸፉ ወደ አገራቸው ሄደው አራብቶታል። በአንጻሩ ደግሞ እውነተኛውን የምሥራቅ አፍሪካ ህዝቦች ማንነት የጸፉም አሉ። ከጥንት ደብተራዎችም አንዳንድ እውነታ ያለውና ወይም ለእውነት የቀረቡ መልዕክቶችን አስተላልፈው ያለፉም አልጠፉም። ይህ ደግሞ ሁሉም ደብተራዎች ሐባሻች ያለመሆናቸውን ያስገነዝባናል። ብዙ የኩሽ ነገድ የሆኑ ደብተራዎች አሉ። ለምሳሌ ተክለ እየሱስ (ነገሮ) የተባሉት በጎጃም የታዋቀ ሰዓሊ የነበሩና የቤተክህነትን ህንጻዎች የውስጥ ገጽታ በሥዕል ሲያሸቆጠቁጡ የነበሩ ሰው ኦሮሞ ናቸው።

እንዲሁም በተለያዩ ቀደምት ገዳማት ውስጥም ብዙ ኦሮሞች ነበሩ። ብዙ እውነተኛ ታሪክ ጽፈው አልፈዋል።

ኣሁን ወደተነሳሁለት የመልስ መልስህ ልመለስና፡ በጽሁፍህ ውስጥ እስኪ ይህችን እንደገና እያት። *"...በሰፊው ተገልጧል እንዴት እንዳልተረዳኸው ገርሞኛል ልብ ብለህ አንብብ ሲጀመር ይህ ተፈጽሟል የተባለው ግፍ እመነኝ ፍጹም ፈጠራ ነው ለምን እቦታው ሔደህ ታሪክ የሚያውቁትን የኦሮሞ ሽማግሎችን አትጠይቅም? ይሔንን የሚልህ አንድ እንኳን ታገኛለህ? በጠላት ለትፋት ዓላማ የተሰበኩት ካልሆኑ በስተቀር እውነቱን የሚናገሩቱ አንዳቸውም እንኳን ተፈጽመዋል አይሉም "* ይላል።

እኔ እንኩዋን በቦታው ሄጄ ብዙ ሽማግሌዎችን የጠየቅሁና ከዚያም አልፈው ብዙ ትምህርት ያገኘሁበት ነው። የብሄሩም አባል ስለሆንኩ ጉዳዩን በጥልቀት ለማዋቅ ችያለሁ። አንተስ ሰሞኑን በሐውልቱ ምርቃት ላይ ሲናገሩ የነበሩትን የ80 ዓመትና ከዚያ በለይ እንድሜ ያላቸውን ሽማግሌዎች ለህዝባቸው የነገሩትን ታሪክ አዳምጣሃልን? እነዚያ ሽማግሌዎች ዋሽተዋል እንደማትለኝ አምናልሁ። ምክንያቱም ሽማግሌዎቹ በወቅቱ ባይኖሩም፡ ከአባቶቻቸውና የቀጥታ የድርጊቱ ሰለባዎች አፍ የሰሙ ናቸውና። ምንም ዓይነት ተቀጽላ መሃላቸው ሳይገባ በኦሮሞ ባህል ታሪክን የማስተላለፍ ዘዴ በመጠቀም ታሪኩን በቀጥታ ከአባቶቻቸው የሰሙትን እነሱም በተራቸው ለህዝባቸው አስተላልፈዋል።

ሌላው ከአንተ ጽሁፍ ውስጥ የታዘብኩኝ እንዲህ ይላል።

*"ይሄንን ስልህ ግን የተቻለውን ያህል የኢትዮጵያን ግዛት ለመመለስ ዐፄ ምኒልክ በዘመቱበት ወቅት የሄዱት ከእንቢተኞችና ከከሀዲያን ጋራ ተዋግተው ግዛቷን ለመመለስ እንጅ ለስብከት አይደለምና በጦርነቱ የተገደሉ የሉም እያልኩህ አይደለም እኔ እያልኩህ ያለሁት ግን ለእኩይ ዓላማው ሲል ፋሽስት ጣሊያን በዚህ የታሪክ እውነታ ላይ መርዘኛ መርዘኛ የፈጠራ ወሬ ጨምሮበታል ነው "*

ምነው ጃል? ልምን ላይ ታች፡ ቅርብ ሩቅ ትሄዳለህ? አንዴ የተስፋዬ ገብረ አብ ልቦዋለድ ትላላችሁ። አንዴ ድግሞ የጣሊያን ልቦዋለድ ሽረባ ትላለህ። ለምን ላለማመን ሰበብ ታበዛላችሁ? እኔ የምመክርህ ደግሞ እውነትን ላለመቀበል "የእናቴ ቀምስ ጠለፈኝ" ብህላችሁን ተውት ነው። እውነት መቸም ብሆን ከቦታዋ አትጠፋምና። በዝህ ላይ የምጨምርልህ ነገር ደግሞ አንተ ለማለት እንደፈለካው ድርጊቱ የተፈጸማው በጦርነቱ የግንባር ውጊያ ሳይሆን በሰላማዊህ ህዝብ፡ በአረጋዊያን ከጦርነት ውጪ በሰላማዊ መንገድ ከቤታቸው ሰብስበው ነው ያንን መስፈሪያ በሌላው ጭካኔ የፈጁዋቸው። መዋቅ ያለብህ ጉዳይ ደግሞ በዚያ ወቅት በኦሮሞች ህግ-ደንብ ሴቶች ህጻናትና ሽማግሌዎች በጦርነት አይሳተፉም። ከጦርነት ቀጣና ይርቀሉ። ስለዚ ምንሊክና የጦር መኮንኖቹ ጦርነቱን በዘመናዊ መሳሪያ የበላይነት ድል ካገኙ በኃላና ሰላም በመጠኑ ከሰፈና ጥቂት ጊዜ ውስጥ ነው። በመሆኑም ሴቶችና አረጋዊያኒኢን ከቤት ጠርተው ነው ድርጊቱን የፈጸሙት።

ይህንን ደግሞ ጣሊያኖቹ ሳይሆኑ ሌሎች በውቅቱ የምንሊክ የጦር አማካሪዎች የሆኑ የውጪ ዜጎች ናቸው። ለምሳሌ የስውስ ዜጋ የሆነው እንጂነር ኤልግ የምንሊክ አማካሪና በኃላ ሚንስቴር የሆነው ግለሰብም መጥቀስ ይቻላል።

ሌላው የአንተ ጽሁፍ ስለአገር ክህደት፡ ስለ አገር መበታተን፡ ስለባንዳነት ሁሉ ሊታስረደንና ሊታሳምነን ሞክረሃል። በተጫማሪ ስለፋሺዝም የተጻፉትን መጽሃፎች እንዳነብ እንድህ በማለት መክረሀኛል። *"እስኪ ፋሺዝም የነበረውን የአገዛዝ ስልት (ስትራቴጂ) የሚያትቱትን መጻሕፍት አንብብ? ሁሉንም እዚያው ትረዳዋለህ  የፋሽስት ጣሊያንን እርኩስነት አረመኔነት ክፋት ሸረኝነት እንዲህ በቀላሉ ለመግለጽ በጣም ከባድ ነው "*

እኔ ግን እንዳማስባው ከአንተ ቀድሜ ስለዚህ ጉዳይ ያነበብኩኝ ይመስላኛል። እንዳማስተውሳውም በኃይላ ሥላሴ ጊዜ ትምህርት ቤት ሆኤን እንዘምር ነበር። ከስንኞቹም አንዱ ስለ ድርጊቱ የሚገልጽ እንዲህ የሚል ነበር። "ኣካፋና ዶማ በደም ተነከረ።" ይል ነበር።

ሌላው የጠቀቀስካው የአምስት ዓመት ከኢጣሊያን ጋር የነበረውን ትግል ብንዘክር እውነቱ እንተ እንደነገርከን ሳይሆን በተቀራኒ መልኩ ነው። በውቅቱ "ንጉሠ ነገሥታችን" በመይጮ ላይ ከተሸነፉ በኃላ ቤተሰቡን ባለሞዋሎቹንና መኮንንቶቹን ይዞ አገሩን ከድቶ ወደ እንግሊዝ አገር ፈረጠጣ። ይህ ከበድ የአገር ክህደት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬ አንተ እራስ የሚታወድሳቸው የነጻነት ሐዋሪያ የሚታደርጋቸው ዘመዶችህ በሙሉና ወደ ሰሜን ያሉ እንዳለ ባንዳ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህ ደግሞ የእናንት ብህል "እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነው።" የሚለውን እንዲናስታውስ ያደርገናል። በወቅቱ የትግሬ መኮንኖች በራስ መንገሻ መሪነት ወደ ሮም ሄደው ለሁምቤርቶ ሞሶሎኒ ተምበርክከው ስግደው የውሸት ሥልጣንና ካባ ተቀብለው ሲመለሱ፡ ከኃይላ ሥላሴ ጋር ሳይሰደዱ በአገር ውስጥ የቀሩ አማሮች ደግሞ አብዛኛው ባንዳ በመሆን ፋኖዎችን ይወጉ ነበር። በውቅቱ አንተ እንደልከው ሳይሆን በአገር ውስጥ ኢጣሊያንን ሲፋለም የነበረው አብዛኛው የኦሮሞ ጀግኖች ናቸው። እስኪ የሩቁን ትተን በሸገር/ፍንፍኔ ዙርያ ብቻ ብንመልከት የእጣሊያንን ሰራዊት የእግር እሳት የሆኑበት በሙሉ ማለት ይቻላል፡ ኦሮሞች ናቸው። በሰሜናዊ ሸገር/ፍንፍኔ በራስ Eበበ ራጋ በቻራ የሚመረው የኦሮሞ ፋኖዎች/አርበኞችን ያቀፈውና እነጄኔራል ታደሣ ብሩ እነ አሰፋ ሻሮ ለሚ የሚገኙበትን፡ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ ሸገር/ፍንፍኔ የኦሮሞ ፋኖዎች/አርባኞች መሪ "የጦሩ ገበሬ" የተባለለት ኦሮሞው ኃይለማሪያም ማሞ፡ በደቡብ ሸገር/ፊንፍኔ በአርበኛው በደጃዝማች ባልቻ ሻፎና ራቅ ብሎ በደቡብ እነ ሊሴ/ደጃዝማች ገብረማሪያም ጋሪ በደቡብ ምዕራብ በፋኖ/አርበኛው መሪ በደጃዝማች ገረሱ ዱኪ የሚመራ የኦሮሞ ጦርና፡ ይህ ጦር ዳግሞ ከአዋስ(አዋሽ) እስከ ኢሉ አባቦራ ጎሬ ድረስ ሄዶ አካባቢውን ከጣሊያን ነጻ ያወጣ አርባኛ ህዝብ ነው።

በምዕራብ ሸገር/ፍንፍኔ ደግሞ በፋኖው/አርባኛው ጄኔራል ጃጋማ ኬሎ ገሮ የሚመራ የፋኖ ጦርና በእነ ደጃዝማች ከበደ ብዙነስ የሚመራም በዚሁ አቅጣጫ ነበር። በዚህ ጊዜነው ለከቤ

አባመርሶ የተዘፈነለት “Kebede Buzunash, goorotti ol dachaase hundumeshii” በማለት ነበር።

ራቅ ካሉት የኦሮሞ አርበኞችና በኃላ በሃይለ ሥላሴ በፍንፍኔ ተክለሃይማኖት አደባባይ በተባለ ቦታ ላይ በገመድ የሰቀለው ጀግና አርባኛ በላይ ዘለቀ የወሎ ኦሮሞና የወሎ ቦረና ጎሣ ነው። ይህ ጀግና በጎጃም ውስጥ ለነበረው ጣሊያን መቅሰፍት የሆና ፋኖ ሆኖ እያሌ በተቀራኒው አማራው ከሃዲና ባንዳ የነበራው ራስ ኃይሉ የተበለ ነበር፡ ይህ ሰው ጣሊያንና ባንዳዎቹን እየመራ በጎጃም ውስጥ የነበሩትን አርባኞች ከማስደብደብ አልፎ እስከ አርባኛው ገረሱ ዱኪ ዞን (የእንቅስቃሴ ቀጠና) በመሄድ አርበኞቹን ከማስመታት አልፎ የአካባቢውን ህዝብ ቤትና ንብረት ሲያቃጥል ነበር። ይህን ዲርጊቱን በዚያ አካባቢ( ድቡብ ምዕራብ ሸገር) ከአዋሽ እስከ ጊቤ ወንዝ ድረስ ከሁለቴ-ሶስቴ ተመላልሰው ፈጽማዋል። ታዲያ ያ የጣሊያን ወረራ በቃል ኪዳን አገሮች በአውሮፓ ውስጥ ሲመታና በእንግሊዝ እርዳታና በጥቅቱ በጠቃቀስኩት አርባኞች አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ የጣሊያን ጦር ተመትቶ ግማሹ ሲማረክ ግማሹ ሲደመሰስ በውስጣቸው የነበሩ የአማራ ከሃዲ ባንዳዎች ገማሹ ሲመረኩ ግማሹ ደግሞ ከስደት ከእንግሊዝ ተጭኖ በሱዳን በኩል ኦሜዲላ በተባለው ቦታ ላለው ኃይላ ሥላሴ እጁን እየሰጣ “እኔ የውስጥ ኣርባኛ ነበርኩ።” እያሉ ምህረት ሲጣይቁና ሹመት ሲቀበሉ ነበር። ከነዚህ ውስጥ አንዱና ቀንደኛ ባንዳ የነበር ራስ ኃይሉ የጎጄሜው ነው።

ኃይላ ሥላሴም ሥልጣኑን መልሰው ከተቆናጠጣ በኃላ እነዚያን  በአምስት አመቱ የአርባኝነት ተግባር የፈጸሙትን ተራበተራ አጠፈፍቶዋቸው ባንዳና ከሱ ጋር ስደታኛ የነበሩትን በዙሪያው ኮልኩሎዋቸው በሥልጣንም አምበሻበሻቸው። በመሆኑም በውቅቱ የአርባኞች እንጉርጉሮ “ኢትዮጵያ አገሬ ተላላ፡ የሞተልሽ ቆርቶ የገደላሽ በላ።” የተባለው ተዜማ። በተጨማሪ ስለ አቡነጴጥሮስ አንስተህ ነብር። ኣዎን! ኦሮሞ ሁሉም ጃግና ነው። በተሰለፋበት መስክ ሁሉ ጀግንነቱን ያስመሰክራል። የአቡነ ጴጥሮስ የትውልድ ስሙ እናትና አባቱ ያወጡለት ሂካ ነው። በያዘው ሃይማኖትም ብሆን በችሎታው ቀዳሚውን ሥፍራ የያዜ ሰው ናቸው። በጀግንነትም የአማራው ቄሶችና ጳጳሳት፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ለፈሺስት ኢጣሊኣን እንዲገብሩ ሲቀሰቅሱና ሲገዚቱ፡ አቡነ ጴጥሮስ ግን የተጣመደበት መትረያስ ሳይፈሩ, የመሣሪያው አፈሙዝ ፊት ቆመው፡ ኢጣሊያንን በማውገዝ አርባኞቹም ትግላቸውን እንዲቀጥሉ ቡራኬ በመስጣት ከሃዲዎችንና ባንዳዎቹን አውግዞዋል።ገዝተዋልም።

ሌላው የጠቀስክልን ስለ ሸገር/ፍንፍኔ የተፈጸመ ድርጊትና የሰማእታቱ ሐውልት የሚመለከት እዲህ ይላል።

*“…የካቲት 12 1929ዓ.ም. ያለቁት ወገኖቻችን ያለቁት የተፈጁት ለኢትዮጵያ ነጻነት፡ ክብር፡ ሉዓላዊነት ሲሉ እንጂ እንደ አሩሲና ሐረር ላይ በጦርነቱ መጀመሪያ ፋሺስት ከዚያም ወያኔና አጋሮቹ ኦነግ ሻቢያ ተቀብለው እያናፈሱ እንዳስወሩት የኢትዮጵያ አካል አንሆንም ለመንግሥት አንገብርም በማለታቸው በግፍ ተፈጁ ብለው ፈጥረው እንደሚያወሩላቸው ይህ መፈጸሙ እውነት ቢሆንም እንኳ “ልብ በል እውነት ነው እያልኩ አይደለም” ኢትዮጵያን ለማፍረስ አንድነቷን ለመበታተን ሉዓላዊነቷን በመዳፈር ለማዋረድ ባለመሆኑ አዎ*

*በትክክልም ሐውልት ሊቆምላቸው ይገባ ነበር ቆሞላቸዋልም  ሁለቱ ፍጹም የተለያዩና የማይገናኙ ነገሮች ናቸው ”*

አሁንም ልነግርህ የሚፈልገው አንተ እንዳልከው እነዚህ የተጨፈጨፉት በነጻነት የግንባር ውጊያ ላይ ሳይሆን፡ ወይም አንተ ደጋግመህ ለመግለጽ እንደሞከርካው የአማራ የነጻነት ታጋዮች ሳይሆኑ፡ በ ፍንፍኔ ውስጥ በሰላም ይሚኖር ህዝብ ሽማግሌ አሮጊቶች ልጆችና አቅማ ደካማ የሆኑትን ህዝብ ነው የፈጀው።  የዚህ ድርጊት ሰበብ ደግሞ ሁለት አገር ወዳድ ወጣቶች አብርሃም ደቦጭና አሳግዶም የሚባሉ ሰዎች በኢጣሊያዊ ጀነራል ጊራዚያን ላይ ቦምብ በመወርወር የመግደል ሙከራ ስለ አደረጉ ነው። እነዚህ ወጣቶች በውቅቱ አምልጠው ነበር፡ ነገር ግን የአማራው ባንዳዎች ይዛው መልሳው ለኢጣሊያኖች አስረክበው አስረሻኑዋቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ በወቅቱ በፍንፍኔ ውስጥ በብዛት ሲኖሩ የነበሩ ከኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ የጉላሌ፡ የኤካና ለሎች የኦሮሞ ጎሣዎች ናቸው። በመጠኑ ደግሞ የነፍጣኛው ጦርና ቤተሰብ፡ በተላያዩ ሰባቦች “ለንጉሡ ነገስታቱ” ቅርባት ያላቸው አዋዳሾችና አሽቃባጮች ናቸው እንጂ ብዙ ብሔር-ቤረሰቦች በብዛት አልነበሩም። ስለዚህ የግራዚያኒ ጦር ህዝቡን አታለው ሰብስበው በመታረያስና አውቶማቲክ መሣሪያ ፈጁት። በቤቱ የተረፈውን አቅማደካሞችን ከነጎጆያቸው በር ዝግቶበት አቀጣሉዋቸው። ስለዚህ የዚህ ድርጊት ሰለባ የሆኑት ባአብዛኛው የጉለሌና ኤካ የኦሮሞ ጎሣዎች ናቸው።

ስለዚህ አንተ በኢትዮጵያዊነትህ በጣም አዛኝ ሆነህ እራስህን ሲታቀርብ፡ እኔን ግን እንዳላዘንኩ አድርገህ ለማቅረብ ሞክረሃል። ወይም እንደካሃዲ ጎራም ሊትፈርጀኝ ዳዲታሃል። ለሁሉም ግን እውነተኛው ታሪክ ግን ሃቁ የት እንደሆነና ፍርዱንም እንድሚሰጥ እተማመናለሁ።

ስለዚህ ምንሊክ በአሮሞች ላይ የፈጸመውና ግራዚያኒ በፍንፍኔ ውስጥ የፈጸመው ተግባር ተመሳሳይ ናቸው። ሁለቱም በሰለም ቦታ ሰላማዊ ህዝብ ላይ ተመሳሳይ ወንጀል ፈጽማዋል። የዘር ማጥፋት ድርጊት ፈጽማዋል። ብታምንም ባታምንም የኦሮሞ ህዝብ ምንሊክን የሚመለከተው እናንተ ግራኝ አህመድን እንደሚትመለከቱት ነው። እናንተ ግራኝ አህመድን በሚትመዝኑት ሚዛን የኦሮሞ ህዝብም ምንልክን ይመዝናዋል። ምክንያቱም ግራኝ አህመድ የእናንተን ሁላንተናዊ ትቁዋማት እንዳጠፋ ሁሉ፡ ምንሊክም የኦሮሞን ሁላንተናዊ ተቁዋማትን አውድሞዋልና። ስለዝህ ነው ለግራኝ አህመድና ለግራዚያን ሐውልት እንደልትሰራለትና፡ እንዳይሰረም እንድሚትፈልጉ ሁሉ እኛም በኦሮሞ ምድር የምንሊክ ሐውልት እንዲሰራ አንፈልግም። በመንደራችሁ በመንዝና በሳይንቲ ሐውልቱን የመሥራትና የፈለጋችሁትን የማድረግ መብት አላችሁ።

ሌላ አንተ ከጠቀስከው ውስጥ ይህችን እስክ መላልሰህ አንብባት።

*“…ጨፍጫፊ እያልክ ጭፍጨፋን አጥብቂ እቃወማለሁ እያልክ በሌላ በኩል ደግሞ ታፈርሰዋለህ  እንዴት ነው “የጠላቱ ጠላት” ሆኖ ነው ሒሳቡ? እዚህስ ላይ ሰብአዊነትህ እንዴት ሳይታይ ቀረ? ምን ነው ወንድሜ ያውም ለፋሽስት ጣሊያን? ለማንኛውም እኛ*

*ኢትዮጵዊያን ለግራዚያኒ የቆመውን ሐውልት የተቃወምነው ከሕፃናት እስከ አረጋዊያን ያሉ ወገኖቻችንን በግፍ ስለጨፈጨፈ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ፋሺዝምና ተዋናዮቹ ወንጀልና ወንጀለኛ ተደርገው ስለተፈረደባቸው የፋሺዝም ተዋናዮችን ማሰብ መደገፍ ወንጀል ስለሆነም ነው እሽ? አንተም እንደኢትዮጵያዊ ባይቆጭህ እንኳን እንደ ዓለም አቀፍ ዜጋ፡ እንደ የሰው ልጅ አብረኸን ልትቃወም በተገባህ ነበር  በእርግጥ በጠባብነትና አመክንዮ አልባ ዘረኝነት ከተጠቃህ እንዲህ ብሎ ለማሰብ ሊከብድህ ይችላል  ይህችን ነገር ተጠንቀቅባት ”*

እዚህ ላይ ብዙ ማለት ባልፈልግም ግን ጥቂት ማለት እፈልጋለሁ። ይህ የጠቀስከው የግልህ የፖላቲካ ዘመቻ ነው። ማንን መቀስቀስ እንደፈለክና ለማን መልዕክቱን ማስተላለፍ እንደፈልክ እራስህ እውቀው። እኔ ግን የምመለከተው እንደ ርካሽ ታዋቂነትን ለማትረፍ የሚደረግ የፖላቲካ ወይም የሳበካ አካል አድርጌ ነው የሚወስደው። ስለዚህ ግራዚያንና ምንሊክ ለኦሮሞ ህዝብ አንድ ናቸው።

ሌላው ከአንተው ድርሰት የሚከተለውን እንይ።

*“…እንደ ራስ ጎበና ዳጨ ያሉ እድሜ ዘመናቸውን የደከሙት ይሔንን የእርስ በእርስ ችግር ለመፍታት ሲሯሯጡ አይደለም እንዴ? ደሞስ እንዴት አያገባህም ትለኛለህ ወገኖቼ ኢትዮጵያዊያን አይደሉም እንዴ? እንዴት ነው የምታስበው?”* ይላል።

እኔ የማስባው እንደ አንተ ሳይሆን ኣንደራሴ ነው። እኔ የሐባሻ-ኢቶጵያን የማያው በኃይል የተገነበች የብሔሮች እስር ቤት አድርጌ ነው። እኔ የማያው በነፍጥ ኃይል የተቁዋቁዋመች ኢምፓየር እንደሆነች ነው። የአንድም ብሔር ወይም ብሔረሰብ ፍቃድ ተጠይቆ የተገነባ ስለልሆነ የእነ ማርሻል ትቶ አገር(ሰርብ፡ ሞንተኒግሮ፡ኮሶቮ፡ ወዛት) የገጠመው እድል ይገጥማታል ብየ አስባለሁ። ይህን የሚያመጠው ደግሞ አጉል ኢትዮጵያዊ-አክራሪነትና የቀድሞ ሥርዓት ነፋቅነት ነው። እኔ የማስባው ወይም የማያው የጥንት በመጽሀፍ ቅዱስና በታሪክ መርማሪዎች የተመዘገባውን ኢትዮጵያንና ህዝቦች በመልካም ጉርብትናና በህዝቦች እኩልነትና በመከባበር የምሥራቅ አፍርካ ህቦችም ሆኑ መላው አፍሪካ በሰላም አብሮ መኖርና መልካም ብልጽግናን፡ የብሔሮችና ብሄረሰቦች መብት ሙሉ በሙሉ ተከብሮና ምንም አይነት ግጪትና ጦርነት የሌለበት አፍሪካን ማየት እፈልጋለሁ፡ እመኛለሁም። እንድህ ነው የማስባው።

ታሪክን በተመለከተ የደረደርካቸው ዘገባዎች ቀደምት ደብተራዎቻችሁ የደራረቱት ተረት-ተረት ስለሁን ብዙም አያሳስበኝ። ምክንያቱ ከአረብና ከጋዛ ተጠራርጎ መጥቶ አፍሪካዊ-ኢትዮጵያው ለመሆን ስለሚትፍጠረጠፍና እናንተ ኢቶጵያዊ ያልነባረችሁ የሰውን ታሪክ ነጥቃችሁ በምላስ ኃይል ለመኖር የሚትሮጡ ስለሆነ ቀጥሉበት እላለሁ። በተጨማሪ በለፈው ጽሁፌ “ኢትዮጵያ ውስጥ የመገንጠል ጥያቄ ማንሳት ይቻላልን?” ላልከው የሰጠሁህን አስተያየት አምብብ።

እስኪ ሌላ የንተን የጽሁ አካል እንመልከት።

“ጠላት ነው ስም የሚያጠፋው እንጂ አማራ ይሄንን ያህል የሠለጠነ አስተዋይና ብሩክ በእግዚአብሔር ቃል የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው  ለም የእርሻ መሬቱን አስረክቦ አሳልፎ ሰጥቶ ለእርሻ ቢሉት ለኑሮ በማይመቸው ተራራ ላይ የሰፈረ ምስኪን ሕዝብ  እስኪ ጠላት ተጨቁናቹሀል ተረግጣቹሀል ተበዝብዛቹሀል የሚላቸውን ብሔረሰቦች የሰፈሩበትን ቦታ ተመልከት ለሙን ሀገር የያዘው ማን ነው? ጠላት እንደሚያወራው አማራ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ዓይነት የመሬት አሠፋፈር ይኖር ነበር ብለህ ትገምታለህ? እባካቹህ ፈጣሪ ይታዘባቹሀል ግፍን ፍሩ?”

እዚህ ላይ በኔ ግምገማ የአማራ ብሄር አትመስልም። በአማራ ስም የሚነግዱ አማራ የባሰውን በሌሎች እንዲጠላ የሚጥሩ የፖላቲካ ነጋዴ የጸፈው ይመስላል።  ከላይ እንደገልጽኩኝ የሐበሻ-ኢትዮጵያ የተመሰረተችው በነፍጥ ኃይል ነው። በመሆኑ ህዝቦችን ሲትወሩ ለወታደራዊ ጠቀሜታ የሆኑትን ቦታዎች እየመረጣችሁ ሰፈራችሁ። ይህም ደግሞ በውቅቱ የኦሮሞን ፈረሰኛ ጦር በመሸሽ በየተራራና በየጉጣጉጥ ተሻጉጣችሁ ነው እንጂ ወዳችሁ ራርታችሁ አርደለም። ይህን የወታደራዊ መሬት ይዞታ አሰራር የእነንተ ድብተራ  ብላቴ ጌታ ማህተመ ሥላሴ የጸፉትን “ዝክረ ነግር” የሚለውን መጽሐፍ እምብብ።

በሌላ በኩል የእናንተ በኣሁኑ ጊዜ አጉል አክራሪነትና የቅድሞ ሥርዓት አቀንቃኞች ድርጊት ብዙ ብሄሮችን እያነሳሳ ነው። በተጨማሪ ኢትዮ-ሪፖርተር የተበለው ድህረገጽ ይዞ ከወጠው ጽሁፍ ውስጥ እንዲህ ይላል።

“…በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር ዞን በስምንት ወረዳዎችና በ128 ቀበሌዎች ውስጥ ሠፍሮ እንደሚገኝ የሚገለጸው የቅማንት ብሔረሰብ፡በማንነትና በራስ አስተዳደር ዙሪያ ላቀረበው ሕገ መንግሥታዊ ጥያቄ፡ ‹‹የክልሉ መንግሥት የሰጠው ምላሽ አግባብነት የጎደለው ነው›› በሚል የካቲት 9 ቀን 2006 ዓ.ም. የተቃውሞ ለሠላማዊ ሠልፍ ማድረጉን አስታወቀ።

የኩሽ ሐረግ ካላቸው ሕዝቦች መካከል አንዱ መሆኑንና የራሱ መገለጫ የሆነ ቋንቋ፡ ታሪክ፡ ወግና ልማድ ያለው ሕዝብ መሆኑን የሚገልጸው ኮሚቴው፡ በታሪክ ጐልቶ እንደሚታወቀው የኦሮሞ ሕዝብ የገዳ ሥርዓት፡ የቅማንት ብሔረሰብም ‹‹ወንበር›› በሚባል የአስተዳደር፡ ባሕላዊና ፖሊቲካዊ አመራር የሚታወቅ መሆኑን አስረድቷል።

የክልሉን ምክር ቤት ውሳኔ በመቃወም በመስከረም ወር 2006 ዓ.ም. ለፌደሬሽን ምክር ቤት ይግባኝ ማለቱን የገለጸው ኮሚቴው፡ በዕለቱ የካቲት 9 ቀን 2006 ዓ.ም. በጎንደር ከተማ ለመጀመርያ ጊዜ ባካሄደው የቅማንት ብሔረሰብ የማንነትና የራስ አስተዳደር ጥያቄ ሰላማዊ ሠልፍ ላይ ከ300 ሺሕ በላይ ሕዝብ መገኘቱን ጠቁሟል። ብሔረሰቡ ጥር 4 ቀን 2006 ዓ.ም. በጭልጋ አይከል ከተማ ባደረገው ሰላማዊ ሠልፍም ከ70 ሺሕ በላይ ሕዝብ መገኘቱንም አክሏል   በጎንደር በተደረገው ሰላማዊ ሠልፍ ላይ የክልሉ መንግሥትም ሆነ ተወካዮች አለመገኘታቸው እንዳሳዘነው ኮሚቴው ገልጿል።”

ይህንንስ እንዴት ታያዋለህ? የወደፊቱስ ሁኔታ ምን የሚሆን ይመስለሃል?

በሊላ በኩል ደግሞ ሰሞኑን አለም አቀፍና የአገር ውስጥ የመገናኛ ብዙሃን እንደዘገቡት ከአማራ ክልል የቅማንትን ብሔር ከደቡብ የኢትዮጵያ ህዝቦች የዶርዜ ብሄረሰብ ጨምረው 19 ቤሄር-ብሔራሰብ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት መመልከቻ አስገብተው ስለማንነታቸው እየተፋለሙ ናቸው።

በእኔ በኩል እንድምገመግማው የሁሉ መዘውር የያዘው የትግራይ ወያኔ ሆኖ እያለ የእናንት ሕዋሃት ትታችሁ ኦሮሞ ላይ መረባረብ ጉዳይ “አህያውን ፈርቶ ዳውላውን” እንድሚባለው ዓይነት ነገር ሆነብኝ።

ሌላው የጽሁፍህ አካል የሆነውና ስለ ፕሮፌሶር መሐመድ ሽምሰድን ነው ብለህ አንድ

የእንግሊዚኛ ግጥመ ጠቅሰህ ነበር። እኔም ቀንጨብ ላድርግልህና የምላው አለኝ።

“He who slept with Galla women is condemned,

because he is considered,
unholy and unclean for sleeping with an Animal,
but if she is converted to Amhara, she will be clean”

ይህ ጽሁፍ የተተረጎመው ከአማሪኛው ጽሁፍና በተስፋ ግብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ የተጻፋና በኦርቶዶክ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተመ “መዝገበ ጸሎት” የሚል መጽሀፍና “ራዕይ ማሪያም” በሚለው ርዕስ ሥር የተጻፈ ነው።

እንዲህ ይላል ።” ወደታች አምስት ሺህ ዓመት ወደላይ አምስት ሺህ አመት የሚያስኬድ ገደል አየሁ። ይህ ምንድር ነው? ብዬ ልጄን ጠይቅሁኝ። እሱም አለኝ። ይህ ቦታ ከጋላ፡ ከእስላም። ከሻንቅላ፡ ከከብት፡ መርገምትዋ ከመጣ ሴትና ከአራስ ጋር የሰስኑና ግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረጉ ሁሉ የኩነኔ ቦታቸው ነው።” ይላል።

እንግዲ የእናንት ማሪያም ይህን ሁሉ ታውቅ ነበር ማለት ነው። ለምሳሌ እሱዋ ከነበረችበት ዘመን ወደ ፊትወይም 600 ዓመት ወደ ኃላ ቀርቶ የተፈጠረውን የእስልምና ሃይማኖት እንድሚመጣ ታውቅ ነበር ማለት ነው። እንዲሁማ “ጋላና ሻንቅላን ከብሔሮች ሁሉ ለይታው ታውቅ ነበር ማለት ነው። ይብላኝ ለእናንተ ሃይማኖታችሁን በራሳችሁ ያዋረዳችሁና ያራከሳችሁት።

እንዲሁም በጽሁፎችህ መጨረሻ አካባቢ ስለ ሃይማኖትና ስለ ኢየሱስ ማንነት ለክርክር ጋብዝሃን ነበር። በኔ አመለካካት የሃይማኖት ጉዳይ አለምን አፈጂቶታል. አሁንም አለ። በኢትዮጵያ ውስጥም የነበረው እራስ ጠቃቅሳሃል። ነገር ግን እናንት የሚትመጻደቁባት ኦርቶዶክ በተክርስቲያ ተልከውን የሳተና የጣኦት መነሃሪያ ሆነ። የሃይማኖቱ መማሪያ መሠረት መጽሀፍ ቅዱስ ሆኖ እያሌ የእናንት ደብተራዎች ህልማቸውና ምኞታቸውን ጽፈው ማስተማሩን አጣደፉት።

ለምሳሌ መጽሀፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 20፡1-17 እና ዘጸ 23፡14-19 ዘደ 7፡1-5 16፡1-7) ተመልከት፡

“እኔ ኣግዚኣብሄር ቀናተኛ ኣምላክ ስለ ሆንሁ ከኔ በቀር ለሌሎች አማልክት አትስገዱ።... የማንኛውንም ዓይነት ምስል ጣኦት ኣድርገህ አትሥራ።” ይላል

ታዲያ የእናንት ያ ሁሉ ሥዕላ ሥዕል ምን እንበለው። የስንቱን ሰዎች ስዕልና ጽላት ተቅርጾ ሲሰገድለት ተኖራ።አሁንም እየሰገዳችሁለት አለችሁ። በአሁኑ ጌዜ 350,000 ጽላት በኢትዮጵያ ውስጥ እንደለ ይገመታል። የሙሴን ሳይጨምር ማለት ነው፡ እግዚኦ አውጠኝ አምላኬ።

በመሆኑም ሃይማኖትን የመጨቆኛ መሣሪያ አድርጋችሁ አገሪትን ሲታሚሱ ቆያችሁ።

ያ ሥርዓታችሁ በደርግ አፈርዲሜ ሲግጥ በሌላ ዞራችሁ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለመፈናጠጥ ተቻኩላችሁ።

ባጠቃላይ ችግሩን በተለያዩ ነገሮች ሸፍናችሁ, እውነቱን ደብቃችሁ እንኖራልን ብትሉ አያዋጣምና ወደ ሁሉን የሚያስታርቅ መፍትሄ ብትፈልጉ ይሻላል። ስለዚ ነገሩ “ኣለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ” ይሆናልና አጉል ትምክህትና አያዋጣምና ብልጥ ሁኑ።

ቃሉ ኩማ